**የአውሮፓ ሕብረት**
**የምርጫ ታዛቢ ልዑክ በኢትዮጵያ 2002 ዓ.ም.**
**የሕዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ**

**ለአስቸኳይ መግለጫ**

## ጋዜጣዊ መግለጫ

**አዲስ አበባ፣ ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም.**

## ስልሳ (60) የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ኢትዮጵያ ስለመድረስ

ስልሳ (60) የአውሮፓ ሕብረት የአጭር ጊዜ ታዛቢዎችን የያዘ ቡድን ቅዳሜ ግንቦት 7 ቀን 2002 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ይደርሳል፡፡ ይህም ቡድን ከዚህ ቀደም በመላው የሀገሪቱ ክልሎች የተሰማራውን ዘጠና (90) የረዥም ጊዜ ታዛቢ ቡድን ይቀላቀላል፡፡ የአጭር ጊዜ ታዛቢ ቡድኑ በአዲስ አበባ የሁለት ቀናቶች ቆይታ የሚያደርግ ሲሆን በምርጫ ሂደት የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ገለጻ ይደረግለታል፡፡

የአጭር ጊዜ ታዛቢ ቡድኑ ወደየኃላፊነት ቦታቸው ሲሰማሩ እንደ ረዥም ጊዜ ታዛቢ ባልደረቦች ከአካባቢ የምርጫ አስፈጻሚዎች፣ እጩዎች፣ ከፓርቲ ተወካዮች፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና መራጮች ጋር ትውውቅ ያደርጋሉ፡፡ የምርጫ ቅስቀሳውን የመጨረሻ ዕለቶች ይታዘባሉ፡፡ እንዲሁም ክሶች፣ አቤቱታዎችንና የምርጫ ዝግጅቶችን ይከታተላሉ፡፡ ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. በምርጫው ዕለትም የረዥምና የአጭር ጊዜ ታዛቢዎቹ የምርጫውን ሙሉ ሂደቶች፣ ከምርጫ ጣቢያው መከፈት እስከ ድምጽ አሰጣጡ፣ ከፍጻሜው እስከ ቆጠራው ይታዘባሉ፡፡

ሁሉም ባለ ሰባ አምስት (75) ሁለት አባላትን የያዙት የታዛቢ ቡድኖች በየምርጫ ክልሉና በፌደራል ደረጃ የሚደረጉ የምርጫ ውጤት አሰባሰብና ይፋዊ አገላለጹን ይታዘባሉ፡፡

በአጠቃላይ ከሀያ ዘጠኝ (29) ሀገራት የተውጣጡ ዋና የቡድኑ አባላትና ሌሎች ዕውቅና የተሰጣቸው የልዑኩ አስፈጻሚዎችን ጨምሮ አንድ መቶ ሰባ (170) የሚሆኑ የአውሮፓ ሕብረት ታዛቢዎች በምርጫው ዕለትና በማግስቱ የሚደረጉ ሥነ-ሥርዓቶችን ይከታተላሉ፡፡ የታዛቢዎቹ ግኝትም የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ልዑክ የሂደቱ አጠቃላይ ምዘናና ግምገማ አካል ይሆናል፡፡

የአጭር ጊዜ ታዛቢዎች ስምሪት በተሽከርካሪ መኪና መጓዟና የአንዳንድ ቡድኖች የአውሮፕላን ጉዞን ያካትታል፡፡ በተሽከርካሪ መኪና የሚጓዙ ቡድኖች ሰኞ ግንቦት 9 ቀን 2002 ዓ.ም. ከሂልተን ሆቴል በስተጀርባ ከሚገኘው የመኪና ማቆሚያ ስፍራ ይነሳሉ፡፡

የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ልዑክ ትክክለኛ ሰዓታቸውን ለመገናኛ ብዙሃን ያሳውቃል፡፡

ግንቦት 9 የአጭር ጊዜ ታዛቢዎች ከተነሱ በኋላ ከአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ልዑክ ዋና ታዛቢ ቲዝ በርማን ጋር ቃለመጠይቅ የማድረግ ዕድል ይኖራል፡፡

ለመገናኛ ብዙሀን ጥያቄዎች ወ/ሮ አግነስ ዶካን ያነጋግሩ
ስልክ፡- +251 (0) 920 537 623
E-mail : agnes.doka@eueom-ethiopia.orgሰሰ